የኢትዮጵያ ወዝ–አደሮች የመኖር ሕልውናቸው፣ የትግል መሣሪያቸው የሆነውን የመደራጀት መብታቸውን እንዳያካሂዱ በልዩ ልዩ የፕሮፓጋንዳና የጦር መሣሪያ ተጽዕኖ ወጥመድ ዓይነተኛው የ ፋሺስታዊ ገዢዎች መለያ ነው:: ይህ ዓይነቱ ድርጊት ወታደሩን ከሕዝቡ አራርቆ የርስ በርስ እልቂት ለማስከተል የሚደረግ ተንኮል መሆኑን ወታደሩ መረዳት አለበት:: ስለዚህ ሰፊው ወታ ደር ለራሱም ሆነ ለሰፊው ሰፊ ሕዝብ የትግል መሣሪያ የሆኑት የ ስብሰባ፣ የመናገር፣ የመፃፍ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና የመደራጀት ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ ከመደብ ጓደኞቹ ጋር ተባብሮ መታገል አለበት::

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ የሚታገልለት ድል እንደተቃረበና የአድሀሪያን አምባገነንነት ውድ ቀት እንደተፋጠነ ለማየት አያስቸግርም:: ሰፊው ወታደር የሰፊውን ሕዝብ የትግል ጉዞ ተመለ ከቶ በጨቋኝ ገዢዎች መቀያየር ሳይወናበድ፣ በአጓጉል ቱልቱላ ሳይደለል ከሌሎች የሰፊው ሕዝብ መደብ ጋር በመተባበር ለሕዝባዊ አብዮት ብሎም ለሰፊው ሕዝብ መንግሥት መታገል አለበት:: አለበለዚያ ራሱንም ወገኑንም የኢምፔሪያሊስቶች የጦር መሣሪያ መነገጃ፣ የሥልጣን ሰሰኞች መሣ ሪያ ያደርጋል:: በየቦታው የሚደረገው ሕዝባዊ እንቅስቃሴና ትግል የሚያሳየው ከሕዝቡ የተ ነጠለና በሕዝቡ ያልተወከለ መንግሥት ዘለቄታ እንደሌለው፣ ለውጥም ለማምጣት እንደማይችል ነው::

ለውጥ ለመምጣት የሚችለው ራሱ የለውጡ ባለቤት /ሰፊው ሕዝብ/ ተደራጅቶ በትግል ራሱን በራሱ ለመምራት ሲችል እንጂ በጥቂት አምባ ገነኖች ምኞትና ፍላጎት አይደለም::

ሰፊው ወታደር የጨቋኝ ገዢዎች
መሣሪያ መሆኑን ያቁም፣

የድል ጉዞ ቀጥሏል፣

የሰፊው ሕዝብ ትግል ያቸንፋል::!